**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות לבתי ספר על־יסודיים

מועד הבחינה: קיץ תשע"ה, 2015

**מספר השאלון: 029109**

**תרגום לאמהרית (6)**

# תולדות עם ישראל בדורות האחרונים

**לעולים חדשים**

**בבתי ספר דתיים**

**חלק ב**

יחידת לימוד אחת

**הוראות לנבחן**

א. <u>משך הבחינה</u>: שעתיים.

ב. <u>מבנה השאלון ומפתח ההערכה</u>:

בשאלון זה שלושה פרקים.

| | | | |
|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — | (15x4) — | 60 נקודות |
| פרק שני | — | (13x2) — | 26 נקודות |
| פרק שלישי | — | (14x1) — | 14 נקודות |
| | סה"כ | — | 100 נקודות |

ג. <u>חומר עזר מותר בשימוש</u>:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

ד. <u>הוראה מיוחדת</u>:

הבא בתשובתך <u>עובדות</u>, ואל תסתפק בהערכות כלליות.

כתוב <u>במחברת הבחינה בלבד</u>, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב <u>כטיוטה</u> (ראשי פרקים, חישובים וכדומה).

רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**ב ה צ ל ח ה !**

**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ወቅት፦ የ2015 ዓ.ም. የበጋ ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 029109**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የሕዝበ እስራኤል ታሪክ በኋለኞዎቹ ትውልዶች

**ለአዲስ ገቢዎች**

**በሃይማኖተኞች ት/ቤቶች ለሚማሩ**

**ክፍል ב**

ባለ አንድ ነጥብ ትምህርት

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

א.<u>ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ</u>፦ ሁለት ሰዓት።

ב.<u>የፈተናው መዋቅርና የነጥብ አሰጣጥ</u>፦

ይህ ፈተና ሦስት ምዕራፎችን ይዟል።

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ — | (4x15) – | 60 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት — | (2x13) – | 26 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሦስት — | (1x14) – | 14 ነጥብ |
| | በአጠቃላይ – | 100 ነጥብ |

ג. <u>ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ</u>፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד.<u>ልዩ መመሪያዎች</u>፦

በመልስህ ላይ ተጨባጭ <u>እውነታዎችን</u> አቅርብ፥ ጠቅለል ባለ ግምታዊ መልስ አታብቃ።

እንደ <u>ንድፍ</u> (<u>הטיוטה</u>) መጻፍ የምትፈልገውን በሙሉ (ርዕሶችን፣ ስሌቶችንና የመሳሰሉትን) <u>በፈተና</u> <u>ደብተሩ ላይ ብቻ</u>፣ በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ። በእያንዳንዱ የንድፍ ገጽ ላይ ንድፍ ብለህ ከላይ ጻፍ። ማንኛውንም ንድፍ በሌላ ወረቀት ላይ ስትጽፍ ከተገኘህ ፈተናህ "ውድቅ" ሊሆን ይችላል።

**በዚህ መጠይቅ ላይ ያሉ መመሪያዎች ለወንድ እንደተሰጡ መስለው ቢቀርቡም፣ መመሪያወቹ ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

# ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ (60 ነጥብ)

ከ1-7 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አራቱን መልስ። (ለእያንዳንዱ ጥያቄ 15 ነጥብ)

**1.** ሃይማኖተኞች የሆኑት አቅኚዎች (החלוצים הדתיים) ወደ ድርጅታዊ ማህበር (הסתדרות) በመግባቱ በኩል የነበራቸውን ግራ መጋባት አብራራ።

**2.** ከተማርከው የእስላም አገራት ውስጥ አንዱን ምረጥ። በመረጥከው አገር ውስጥ በሁለቱ ጦርነቶች መካከል በሕግ ዘርፍ እና በትምህርት ዘርፍ በኩል የነበረውን የይሁዳዊያን ሁኔታ/ቦታ ግለጽ።

**3.** በሦስተኛው ነጭ መጽሐፍ የብሪታንያ አስተዳደር በእስራኤል አገር የሚኖሩ ይሁዳዊያንን በተመለከተ በነበረው ፖሊሲ ላይ መጥፎ ለውጥ ነበር።
ለመጥፎው ለውጥ መንስዔ ከሆኑት ሁለቱን አብራራ።

**4.** ከ1936 እስከ 1939 (ט"צרת-ו"צרת) ክስተት ምላሽ በሚሰጥበት መንገድ ላይ በይሁዳዊያን ሠፈራ የነበሩትን ሁለት ተቃራኒ አመለካከቶች ጥቀስ እና ለእያንዳንዱ ጎን አመለካከት ማስረጃ አሳይ።

**5.** የ"ዕብራዊያን አማጺያን እንቅስቃሴ"ን "תנועת המרי העברי" ያቋቋሙት የትኞቹ ድርጅቶች እንደሆኑ ጥቀስ እና ለምን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እንዳቋቋሙት አብራራ።

**6.** ሃአፓላ (ההעפלה) ሃገርን ለመመሥረት ለተካሄደው ትግል ረድቷል። ለዚህ ሁኔታ ሁለት ማብራሪያዎችን አቅርብ።

**7.** የነፃነቱ ጦርነት በእስራኤል አገር ድንበሮች ላይ ተፅዕኖ አድርጓል። ይህንን ዐረፍተ ነገር በሁለት ምሳሌዎች አማካኝነት አብራራ።

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

## ምዕራፍ ሁለት (26 ነጥብ)

ከ8-11 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱን መልስ። (ለእያንዳንዱ ጥያቄ 13 ነጥብ)

**8.** የ"ריבנטרופ-מולוטוב" ስምምነት እስከ 1941 ዓ.ም. በፖላንድ በነበሩ ይሁዳዊያን ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንዳደረገባቸው አብራራ።

**9.** በሄይድሪሀ "ኢጌሬት ሃቤዜክ" "איגרת הַבזק" መሠረት ናዚዎች ዮደንራት (יודנראט) ይሆኑ ዘንድ የተከበሩ ሰዎችንና ራባናትን መረጡ።
ናዚዎቹ በእንደእነዚህ ዓይነት ሰዎች ላይ ፍላጎት ያደረባቸው ለምን እንደሆነ አብራራ።
በ"איגרת הַבזק" መሠረት የዮደንራትን አንድ የሥራ ድርሻ ጥቀስ።

**10.** በ"ሾአ" የነበሩት ይሁዳዊያን በሕይወት ለመኖር ትንቅንቅ ገጥመዋል እናም ይሁዳዊያን ሆነው ለመቅረትም ትንቅንቅ (ትግል) ገጥመዋል።
ይህ እያንዳንዱ ትንቅንቅ ለምን ናዚዎችን የመቃወሚያ መግለጫ ሆኖ ሊታይ እንደሚችል አብራራ።

**11.** በ"ሾአ" ወቅት በ"ጌቶ" አማጺያን ላይ የነበሩባቸውን ሁለት ችግሮች አሳይ።

## ምዕራፍ ሦስት (14 ነጥብ)

ከ12-13 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**12.** በ1950ዎቹ ዓመታት ወደ እስራኤል አገር መግባቱን (עלייה) ውስን እንዲሆን የደገፉ ነበሩ የተቃወሙም ነበሩ።
ለእያንዳንዱ አመለካከት አንድ ማብራሪያ አቅርብ (በአጠቃላይ – ሁለት ማብራሪያዎች)።

**13.** ሃገረ እስራኤል ከተቋቋመች በኋላ በሠፈራ ላይ የተጀመሩትን ሁለት ለውጦች አሳይ።

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ የእስራኤል መንግሥት ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך